# የገንዘብ ሚኒስቴር

## መመሪያ ቁጥር 1039/2017

## የሰቀጣ ቃልኪዳን ፋይናንስ አስተዳደር

ጥር 2017 ዓ.ም
የገንዘብ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

Uploaded on the website of the Ministry of Finance on 28 January 2025

# የሰቆጣ ቃልኪዳን ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ

ለሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮግራም ማስፈጸሚያነት ከመንግስት የሚመደብ በጀት ወጥ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት ጠንካራ የፋይናንስ አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የገንዘብ ሚኒስትሩ በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሰቆጣ ቃልኪዳን ፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1039/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ "**የሰቆጣ ቃልኪዳን**" ማለት እድሜያቸው ከሁለት ዓመት በታች በሆኑ ህፃናት ላይ የሚከሰተውን መቀንጨር ለመከላከልና ለማጥፋት ሐገሪቷ የገባችው ቃልኪዳን ነው፤

2/ **"መቀንጨር"** ማለት ሥር-የሰደደ የስርዓተ-ምግብ ችግር ሲሆን ከህፃናት ፅንሰት ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ባሉት ግዜያት ውስጥ የሚከሰት የአካልና የአዕምሮ ዕድገት መገታት ነው፡፡

3/ "**በጀት**" ማለት ለሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮግራም ማስፈጸሚያነት ከመንግስት የሚመደብ፣ ከለጋሽ ድርጅቶች ወይም ሌሎች አካላት የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው፤

4/ **"አቻ ፈንድ"** ከፌዴራል መንግስት ከሚተላለፈው በጀት እኩል በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች  ለፕሮግራሙ የሚመደብ በጀት ነው፡፡

5/ **"የሚኒስትሮች ጥምር ኮሚቴ"** ማለት የምግብና ሥርዓተ-ምግብስትራቴጂን ለማስተባበር በመንግስት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

6/ **"ተቋም"** ማለት የሰቆጣ ቃልኪዳን ማስፈጸሚያ በጀት የሚተላለፍላቸው የመንግስት መ/ቤትነው፤

7/ **"የማስተባበሪያ ጽ/ቤት"** ማለት በክልል ርዕሰ-መስተዳድር እና በከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ስር የሚገኝ የምግብ ስርዓት፤የስርዓተ ምግብ ስትራቴጂንና የሰቆጣ ቃል ኪዳንን ትግበራ የሚያስተባብር ጽ/ቤት ነው፡፡

8/ **"ሚኒስቴር** ወይም **ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የሚኒስቴሩ ሚኒስትር ነው፤

9/ **"የብሔራዊ ክልላዊ መንግስት"** ማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47 የተቋቋመ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

10/ **"የክልል ፋይናንስ ቢሮ"** ማለት የክልል እና የከተማ መስተዳድሮች ደረጃ የመንግስት ፋይናንስን የሚመራ ቢሮ ነው፤

11/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

12/ በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንቡ ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ላይ ጥቅም ላይ ከዋለ በእነዚህ ሕጎች የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

13/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮግራምን በሚተገብሩ የፌደራል እና የክልል ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሰቆጣ ቃልኪዳን ፋይናንስ አስተዳደር</u>

4. <u>በጀት</u>

1) የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፋይናንስ በመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች እንዲሁም በመንግስት ግዥ አዋጅ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) የሰቆጣ ቃልኪዳን በጀት በፌዴራል በጤና ሚኒስቴር፣ በክልል በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት "አቻ ፈንድ" በበጀት ይያዛል፡፡

3) ለኘሮግራሙ የተመደበው በጀት በጥሬ ገንዘብ ዕቅድ መሰረት ለፌዴራልና ለክልል አስፈጻሚ መ/ቤቶች ይተላለፋል፣ ለአስተዳደራዊ ወጪ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች የወጪ በጀት ይመደባል፣

4) የኘሮግራሙ ሂሣብ በየሶስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይቀርባል፣ይመረመራል፣

5. <u>የጥሬ ገንዘብ መሰብሰቢያ ገቢ ደረሰኝ አመዘጋገብ</u>

የሰቆጣ ቃልኪዳን ፈፃሚ ተቋማት በባንክ ለሚተላለፍለት ገቢ ከባንክ የሚሰጣቸው አድቫይስ ወይም ስሊፕ ተጠቅመው በገቢ ደረሰኝ መሰብሰቢያ መሂ-1 የሂሳብ ምዝገባ መከናወን አለበት።

6. <u>ስለ ቁጥጥር እና ኦዲት</u>

ለክልልና ከተማ አስተዳደር ለሰቆጣ ቃል ኪዳን የተመደበው ፋይናንስ የሂሣብ ሪፖርት በክልሉና ከተማ አስተዳደሩ ዋና ኦዲት ቢሮ ኦዲት ይደረጋል። ሪፖርቱም ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለጤና ሚኒስቴር እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል።

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

7. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ለሰቆጣ ቃልኪዳን የተመደበ በጀት ለጤና ሚኒስቴር ያሳውቃል፤

2) ከጤና ሚኒስቴር በሚቀርብለት የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ መሰረት ገንዘብ ለጤና ሚኒስቴር እና ለክልልና ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ያስተላልፋል፤

3) ለፌደራል ተቋማት"*ሰቆጣ ቃልኪዳን ኘሮግራም*" በሚል ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ክልሎችም በዚሁ ስም የባንክ ሂሣብ እንዲከፍቱ ያስደርጋል፣

4) ለጤና ሚኒስቴር ወቅታዊ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት ይልካል፣

5) ስለሂሳብ አመዘጋገብ እና አዘጋግ አስፈላጊውን ማብራሪያ ለተቋማት ያስተላልፋል።

8. <u>የጤና ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የሰቆጣ ቃልኪዳንን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፣ለሚኒስትሮች ጥምር ኮሚቴ አፈፃፀሙን በሚመለከት ሪፖርት ያቀርባል፣

2) በሚኒስትሮች ጥምር ኮሚቴ በጸደቀው በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ መሰረት የሚያስፈልገውን ዓመታዊ የበጀት ጥያቄ ለገንዘብ ሚኒስቴር ያቀርባል፤

3) በጸደቀው በጀት መሰረት ወቅታዊ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር የክፍያ ጥያቄ ያቀርባል፣

4) ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች የፀደቀውን በጀት መሰረት በማድረግና በዝርዝር የስራ መርሀ-ግብሩ መሰረት የበጀት ድልድሉን ያዘጋጃል፣

5) ለክልልና ከተማ አስተዳደር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የበጀት ዓመቱን የፕሮግራምና የፋይናንስ ዕቅድ ይልካል፤

6) ለክልል/ከተማ አስተዳደር የሰቆጣ ቃልኪዳን አስፈፃሚ አካላት የአቅም ግንባታ ድጋፍ ያደርጋል፤

9. <u>የክልል እና የከተማ አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) በክልልና በከተማ አስተዳደር ምክር ቤት የፀደቀውን በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድና የበጀት ድልድል ከማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንዲላክለት ያደርጋል፣

2) በክልሉና ከተማ አስተዳደሩ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የሚቀርበውን አቻ በጀት (Matching fund) ጥያቄ ገምግሞ ለክልል ምክር ቤት በማቅረብ በጀቱ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

3) የጸደቀውን አቻ በጀት ለክልሉና ከተማ አስተዳደሩ በተከፈተው የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደርጋል፤

4) ከገንዘብ ሚኒስቴር ለተላከለት ገንዘብ በገቢ ደረሰኝ ይመዘግባል፣ ገቢ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፣

5) በሰቆጣ ቃል ኪዳን "ሰቆጣ ቃልኪዳን ኘሮግራም" መደቡ B የሆነ የባንክ ሂሳብ እንደ አስፈላጊነቱ ለሴክተሮች ለዞንና ለወረዳዎች እንዲከፈት ያደርጋል፣

6) የክልልና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤቶች ባፀደቁት ዕቅድ፣ የበጀት ድልድል እና ከማስተባበሪያ ጽ/ቤት በሚላክለት የጥሬ ገንዘብ ድልድል መሰረት ለሴክተር መስሪያ ቤቶችና ለወረዳዎች ገንዘቡን ያስተላልፋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንደ ክልሉና ከተማ አስተዳድሩ ተጨባጭ ሁኔታ በዞኖችን እና ክፍለ ከተሞች በኩል ሊያስተላልፍ ይችላል፤

7) ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፣ ለሴክተር ቢሮዎች፣ ለዞንና ለወረዳ የአቅም ግንባታ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

8) የገቢና ወጪ ሂሳብ በመደበኛው የመንግስት የፋይናንስ አሰራር ስርዓት (IBEX) እንዲከተል ያደርጋል፣ በየደረጃውም በዚሁ መሰረት እንዲከናወን ያደርጋል፤

9) የክልሉን/የከተማ አስተዳደሩን የሂሣብ ሪፖርት በየሶስት ወሩ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይልካል፤

10) ለየአስፈፃሚው የተላለፈውን ፋይናንስ የሂሣብ ሪፖርት እንዲዘጋጅ በማድረግ ኦዲት ያስደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና ሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል፡፡

10.<u>የክልል ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) የክልልና ከተማ አስተዳደር ፈጻሚ ቢሮዎችን፤ ዞኖችንና ወረዳዎችን በማስተባበር ከገንዘብ ሚኒስቴር ለፋይናንስ ቢሮ ለሚተላለፈው ገንዘብ እና በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ለሚመደበው አቻ በጀት ይረዳ ዘንድ በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ለጤና ሚኒስቴርም ለግብአት ያቀርባል፡፡

2) የክልሉን አቻ በጀት (Matching fund) ጥያቄ አዘጋጅቶ ለፋይናንስ ቢሮ በማቅረብ በጀቱ በፋይናንስ ቢሮ በኩል ለምክር ቤት ቀርቦ መጽደቁን ክትትል ያደርጋል፣

3) ለክልሉ የፀደቀውን በጀት መሰረት በማድረግ በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ ዝርዝር የስራ መርሀ-ግብር መሰረት የበጀት ድልድሉን ያዘጋጃል፣

4) የጸደቀውን በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ ከገንዘብ ሚኒስቴር ገንዘብ እንዲጠየቅለት ለጤና ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

5) ከገንዘብ ሚኒስቴር ለፋይናንስ ቢሮ የተላለፈውን ገንዘብ እና የክልሉን አቻ በጀት (Matching fund) ጨምሮ ለሴክተር ቢሮ እና ለወረዳዎች በመደልደል ለፋይናንስ ቢሮ ይልካል፣

6) ከገንዘብ ሚኒስቴር ለፋይናንስ ቢሮ የተላለፈውን ገንዘብ እና የክልሉን አቻ በጀት በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ መሰረት ለታለመለት አላማ ብቻ መዋሉን ክትትል ያደርጋል፤

7) ለየአስፈፃሚው የተላለፈውን ፋይናንስ የሂሣብ ሪፖርት እንዲቀርብ፤ በከፍተኛ አመራሩ እንዲገመገም እና ሂሣቡ ኦዲት እንዲደረግ ክትትል ያደርጋል፡

8) የክልሉን/የከተማ አስተዳደሩን የሂሣብና የፕሮግራም አፈፃፀም ሪፖርት በየሶስት ወሩ እና በበጀት ዓመቱ ለጤና ሚኒስቴር ይልካል፤

## 11. <u>የክልል፣ የዞን እና ወረዳ አስፈጻሚ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1) ከክልሉ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር በበጀት የተደገፈ የወረዳ አቀፍ የብዝሃ ሴክተር ዕቅድ ያዘጋጃሉ፤ በካቢኔያቸው ያጸድቃሉ፤ ለማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ይልካሉ፤

2) የክልል አስፈጻሚ ተቋማት ከፋይናንስ ቢሮ የሚተላለፈላቸውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ በማዋል የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ ኦዲት ማስደረግ እና የፋይናንስና አጠቃቀም ሪፖርት ለፋይናንስ ቢሮ መላክ አለባቸው፡፡

## 12.<u>የወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ከፋይናንስ ቢሮ የተላለፈለትን ገንዘብ በተዘጋጀው ወረዳ አቀፍ የብዝሀ-ሴክተር ዕቅድ መሰረትፈፃሚ ፅ/ቤቶች መጠቀማቸውን ያረጋግጣል፣ የፋይናንስ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፋይናንስ ቢሮ ይልካል፣ ኦዲትም ያስደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በሚኒስቴሩ ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አህመድ ሺዴ**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚንስትር**